አሀዛዊ መረጃ

ICRC

ኢትዮጵያ

# አሀዛዊ መረጃ

## እአአ ከጥር እስከ ታህሳስ 2020



ICRC

የዓለም አቀፍ ቀይ መስቀል ኮሚቴ (ዓአቀመኮ) ስራውን በኢትዮጵያ የጀመረው እአአ በ1977 ዓ.ም በኢትዮጵያና ሱማሌ መካከል ከተካሄደው የትጥቅ ግጭት አንስቶ ነው። የዓአቀመኮ በአሁኑ ጊዜ በአገሪቱ የሚያከናውናቸው ዋና ዋና ተግባራት እስረኞች ዓለም አቀፋዊ ደንቦችንና መስፈርቶችን መሠረት ባደረገ መልኩ ሰብዓዊ ክብራቸው ተጠብቆና ተከብሮ መያዛቸውን ለማረጋገጥ እንዲቻል ማረሚያ ቤቶችን መጎብኘትና  የአካል ጉዳተኞች ማቋቋሚያ ፕሮግራም የአካል ጉዳተኞች የመልሶ ማቋቋሚያ አገልግሎትን በጥራትና በዘላቂነት ለማግኘት እንዲችሉ መርዳት ናቸው። ከኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማህበር (ኢቀመማ) ጋር በመተባበር በትጥቅ ግጭትና በሌሎች ብጥብጦች ምክንያት የተነጣጠሉ ቤተሰቦችን እንደገና ግንኙነት እንዲመሰርቱ ጥረት ማድረግና በግጭትና በብጥብጥ ምክንያት ጉዳት ለደረሰባቸው ሰዎች እርዳታ የመስጠት ተግባርም ያከናውናል። ከዚህ በተጨማሪም ዓለም አቀፍ የሰብዓዊነት ህግ እውቀትን ለመከላከያና ፖሊስ ሀይል አባላት፣ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ለህግ ባለሙያዎችና ለፖሊሲ አውጪዎች ያሰራጫል። እአአ በ2020 ዓ.ም የዓአቀመኮ የሰብዓዊነት ተግባራት በዋናነት ያተኮረው በሁለት ዋና ዋና ጉዳዮች ማለትም በኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ ክስተት ምክንያትና በሰሜን ኢትዮጵያ ውስጥ ለተፈጠሩት ችግሮች ምላሽ በመስጠት ላይ ነው። የዓአቀመኮ እአአ ከመጋቢት ወር 2020 ዓ.ም ጀምሮ ከተከሰተው የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ ጋር ተግባራቱን በፍጥነት በማጣጣምና በማቀናጀት ቫይረሱ ላስከተለው ቀውስ ምላሽ የመስጠት ተግባራቱን እያፋጠነ ይገኛል። በሌላ በኩል ደግሞ እአአ ከህዳር ወር መጀመሪያ 2020 ዓ.ም ጀምሮ  በሰሜን ኢትዮጵያ ለተፈጠረው ችግር ምላሽ በመስጠት ረገድ የዓአቀመኮ በህክምና መድሀኒት አቅርቦት እጦት ምክንያት ክፉኛ ለተጎዱ የጤና ተቋማት የመድሀኒትና የህክምና ቁሳቁሶች በአፋጣኝ ያቀረበ ሲሆን በትግራይ ክልል የተነጣጠሉ ቤተሰቦችን መልሰው ግንኙነት እንዲመሰርቱ የሚያስችል እገዛም አድርጓል። ከዚህም በተጨማሪ የዓአቀመኮ ከኢቀመማ ጋር በመተባበር የተፈናቀሉ ሰዎችን ጨምሮ በተፈጠረው ሁኔታ ጉዳት ለደረሰባቸው ሰዎች የአስቸኳይ ጊዜ እርዳታና የውሀ አቅርቦት አድርጓል።

## ማረሚያ ቤቶች

### እአአ ከጥር እስከ ታህሳስ 2020 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ የዓአቀመኮ

- ቁጥራቸው 72,000 የሚጠጉ ታራሚዎችን ከመጎብኘቱም በላይ 242 ታራሚዎችን በግለሰብ ደረጃ ተከታትሏል። ለ57 ማረሚያ ቤቶች የንጽህና መገልገያዎች፣ አልባሳት፣ ብርድልብሶችና የመዝናኛ መገልገያዎችን ጨምሮ ሌሎች እርዳታዎችን በመስጠት ከ63,000 የሚበልጡ ታራሚዎችን ተጠቃሚ አድርጓል።
- በ38 ማረሚያ ቤቶች የውሀና የጽዳት አገልግሎት መስመሮችን በመገንባትና እና በመጠገን 51,000 ታራሚዎችን ተጠቃሚ አድርጓል።
- 10,940 ታራሚዎች ነጻ የስልክ ጥሪዎችና የአየር ሰዓት አገልግሎት እንዲያገኙ በማድረግ ከቤተሰቦቻቸው ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለማስቀጠል አስችሏል።



Wilson Mondal /ICRC

የኮቪድ-19 በሽታን ለመከላከል ኢንዲረዳው ለጎንደር ማረሚያ ቤት የተሰጠው የግል ንጽህና መጠበቂያ ቁሳቁስ፤ ጎንደር፤ አማራ ክልል (2020 ዓ.ም)።

- ለጉዳት ተጋላጭ የሆኑ የአካል ጉዳተኛ ታራሚዎችን ክብር ለመጠበቅ የሚያስችሉ የግል ንጽህና መጠበቂያና አልባሳት ለ90 የአእምሮ በሽተኞችና ነፍሰጡር ሴቶች ለግሷል።
- በኦሮሚያ ክልል ለሚገኙ የማረሚያ ቤት ሪፈራል ክሊኒኮች የሚሰጠውን የህክምናና የቴክኒክ ድጋፍ ቀጥሏል።
- በተለያዩ የፌዴራልና ክልል ማረሚያ ቤቶች ውስጥ የሚገኙ 43 ለጉዳት የተጋለጡ የአካል ጉዳተኛ ታራሚዎች ፍላጎታቸውን ለማሟላት  እንዲችሉ  የህክምና ነክና ህክምና ነክ  ያልሆኑ ቁሳቁሶችን (የግል ንጽህናና የመንቀሳቀሻ መርጃ መሳሪያዎች) ለግሷል።
- ከ63,000 በላይ ታራሚዎችን ለያዙ 57 ማረሚያ ቤቶች ከ516,000 የሚበልጡ ሳሙናዎች፣ 315 ቋሚ የእጅ መታጠቢያዎች፣ 435 ኪሎ ክሎሪን፣135 ዲስፔንሰሮች እና 330 ሊትር የእጅ ብክለት ማጽጃ ኬሚካል እርዳታ አድርጓል።

- በአዲስ አባባ፣አማራ፣ኦሮሚያ፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ ሶማሌ እና ሲዳማ ክልሎች ለሚገኙ 13 የማረሚያ ቤት ጤና ተቋማት የኮሮና ቫይረስን ለመቆጣጠር እንዲችሉ የብክለት መከላከያ ቁሳቁስ እርዳታ በመስጠት 15,750 ታራሚዎችን ተጠቃሚ አድርጓል።።
- የኮቪድ 19 በሽታን በመከላከልና በመቆጣጠር ላይ ያተኮረ ስልጠና ከመላ አገሪቱ ክፍል ለተውጣጡ 28 የማረሚያ ቤት ጤና ሠራተኞች ስጥቷል።

## የተነጣጠሉ ቤተሰቦች

እአአ ከጥር እስከ ታህሳስ 2020 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ የዓአቀመኮ



የደቡብ ሱዳን ስደተኛ በቅርቡ በቀይ መስቀል በኩል ከተገኘችው እህቷ የተላከ ደብዳቤ ስታነብ፤ጋምቤላ (2020 ዓ.ም)።

- ከኢቀመማ ጋር በመተባበር በአዲስ አበባ፣ ጎንደር፣ሞያሌና ድሬዳዋ ውስጥ ባሉ ሰባት የለይቶ ማቆያ ማዕከሎች ውስጥ ለተቀመጡና ከስደት ለተመለሱ 33,224 ኢትዮጵያውያን የምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች እርዳታ አድርጓል።
- 33,281 ከስደት ተመላሾች ኢትዮጵያ ሲደርሱ ከሚወዷቸው ሰዎች ጋር ግንኙነት ለማድረግ እንዲችሉ የስልክ ጥሪ አገልግሎት አቅርቦት አድርጓል።
- ከኢቀመማ ጋር በመተባበር ስደተኞችና ተመላሾች በየአገሮቻቸው ከሚገኙ ቤተሰቦቻቸው ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለማስቀጠል የሚያስችሉ 56,781 ነጻ የስልክ ጥሪዎች እንዲያደርጉ አስችሏል።
- በኢትዮጵያና ውጪ አገራት የጠፉባቸው ዘመዶቻቸውን በመፈለግ ላይ ካሉ ሰዎች 447 የአፋልጉኝ ጥያቄዎችን የተቀበለ ሲሆን ከእነዚህም መካከል የ378 ሰዎችን አድራሻ አግኝቷል።
- ከኢቀመማ ጋር በመተባበር በግጭትና በብጥብጥ ምክንያት ከተጠፋፉ የቤተሰብ አባላት 6,000 የቀይ መስቀል መልዕክቶችን የሰበሰበ ከመሆኑም በላይ በግጭት ወይም በብጥብጥ ምክንያት ለተነጣጠሉ 1,398 የቤተሰብ አባላት የቀይ መስቀል መልዕክቶችን አከፋፍሏል።
- የተነጠሏቸውን የቤተሰብ አባላት በመፈለግ ላይ ያሉ 396 የደቡብ ሱዳን ስደተኞችን ፎቶዎች የያዙ ሁለት አዲስ ጥራዞችን አሳትሟል።

## ጤና

እአአ ከጥር እስከ ታህሳስ 2020 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ የዓአቀመኮ

- በተለያዩ ክልሎች የሚገኙ 17 የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ጣቢያዎችና 23 ሆስፒታሎች በአስቸኳይ ጊዜ ምላሽ የመስጠት አቅማቸውን እንዲያጎለብቱ መሰረታዊ የጤና መገልገያዎችንና የአስቸኳይ ጊዜ ቁሳቁሶችን የያዙ ሳጥኖችን ለግሷል።
- በሁሴና በጭናቅሰን እንዲሁም በቱሊጉሌድና መዩ ወረዳዎች ለሚገኙ አራት የጤና ማዕከሎች ወርሀዊ የቴክኒክ እገዛ፣የህክምና መገልገያዎች፣ የቅድመ ወሊድ ምግብ ነክ ያልሆነና የልጆች ደህንነት መጠበቂያ ቁሳቁስ እርዳታ በመስጠት በማዕከሎቹ ውስጥ ልጆቻቸውን የተገላገሉ 2,100 እናቶችን ተጠቃሚ አድርጓል። እንዲሁም የዓአቀመኮ የግል የበሽታ መከላከያ ቁሳቁስ (ሽርጦች፣ቦት ጫማዎች፣የእጅ ጓንቶች፣ፈሳሽ ሳሙናዎችና ቋሚ የእጅ መታጠቢያዎች) እርዳታ ከላይ በተጠቀሱት ወረዳዎች ለሚገኙ የጤና ማዕከሎች ሰጥቷል ።
- ለኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ተቋምና ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በኮቪድ-19 ምክንያት የሚሞቱ ሰዎችን አስከሬን በአግባቡ ለመያዝና ለማስተናገድ የሚረዱ አራት ስልጠናዎች ከተለያዩ ክልሎች ለተውጣጡ 2,100 የጤና ባለሙያዎች ለማዘጋጀት የሚያስችል ድጋፍ አድርጓል።
- ከኢቀመማ ጋር በመተባበር በአማራ፣በኦሮሚያ፣አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ ሱማሌና ሀረሪ ክልሎች ውስጥ ለተቋቋሙ 17 የኮቪድ-19 የህክምና ማዕከሎች 2,500 ፍራሾች፣ 2,500 አንሶላዎችና 20,000 ሳሙናዎችና የበሽታ ብክለት ማጽጃ ኬሚካሎች ሰጥቷል።

## የኢኮኖሚ ዋስትና

እአአ ከጥር እስከ ታህሳስ 2020 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ የዓአቀመኮ



በጎሳ ግጭት ምክንያት የተጎዱ ሰዎች መሠረታዊ የቤት ውስጥ ቁሳቁስ እርዳታ ከቀይ መስቀል እርዳታ ማከፋፈያ ጣቢያ ስቀበሉ፤ ኮነሶ፤ደቡብ ኢትዮጵያ (2020 ዓ.ም)።

- በምስራቅና ሐረርጌና በምዕራብ ወለጋ (አርሚያ ክልል)፣ በፋፋንና ኤረር (ሱማሌ ክልል) በካማሺ (ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል) በማህበረሰባዊ ግጭት ምክንያት ጉዳት ለደረሰባቸው 12,350 ቤተሰቦች መልሰው ኑሮአቸውን እንዲመሰረቱ 700 ቶንስ የበቆሎ፤ የማሽላ፣ የአተር፣የጤፍና ስንዴ ዘር እህል እርዳታ ሰጥቷል።
- በቋራ (አማራ ክልል) እና ቱሊጉሌድ፣ራሶና ሳላሃድ (ሱማሌ ክልል) መተከል (ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል) እና በኮንሶ (ደቡብ ኢትዮጵያ ክልል) በማህበረሰባዊ ግጭት ምክንያት ለተፈናቀሉ 7,000 ሰዎች የፕላስቲክ መጠለያዎች፣ ምንጣፎች፣ብርድልብሶች፣ ጀሪካኖች፣ ሳሙናዎችና የምግብ ማብሰያ ቁሰቁሶች እርዳታ አድርጓል።

- በአማራ፣ሱማሌ፣ቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ኦሮሚያ እና በጋምቤላ ክልሎች በጎሳ ግጭት ምክንያት ጉዳት ለደረሰባቸው 26,488 ሰዎች ከ1,000 ብር እስከ 6,000 ብር የሚደርስ የገንዘብ እርዳታ ሰጥቷል።
- በሱማሌና ኦሮሚያ ሰሜናዊ ድንበር አካባቢዎች ለሚኖሩ 450,000 ከፊል አርብቶ አደር ማህበረሰብ የቤት እንስሳዎችን የጸረ እንስሳት በሽታዎች መከላከያ ክትባት (ለአንትራክስ፣ብላክሌግ እና ፓስትሮላ) ለመስጠት የሚያስችል እርዳታ አድርጓል። በዚህም 196,800 ሰዎች ተጠቃሚ ሆነዋል።

## የውሀና መኖሪያ አካባቢ

እአአ ከጥር እስከ ታህሳስ 2020 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ የዓአቀመኮ

- በጭናቅሰን ከተማና በጉርሱም ወረዳ (ኦሮሚያ ክልል) የውሀ አውታርችን በማደስ በብጥብጥ ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸውና ቁጥራቸው ከ52,400 የሚበልጥ ሰዎችን የውሀ አገልግሎት ተጠቃሚ አድርጓል።
- በባቢሌ ወረዳ (ሱማሌ ክልል) የከርሰምድር ውሀ ማጠራቀሚያ ግንባታ ስራን በማጠናቀቅ 4,500 ሰዎችን ተጠቃሚ አድርጓል።
- በአውጃበር ቀበሌ (ሱማሌ ክልል) የውሀ አገልግሎት ፕሮጀክት ግንባታን ያጠናቀቀ ሲሆን ፕሮጀክቱም በብጥብጥ ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸው 10,000 ሰዎችን ተጠቃሚ ያደርጋል ተብሎ ይጠበቃል።
- በሀሮሊሙ ወረዳ (አርሚያ ክልል) እና በያሶ ወረዳ (ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል) ውስጥ ሶስት የውሀ ጉድጓድ ቁፋሮ ስራን በማጠናቀቅ በማህበረሰባዊ ግጭት ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸው 3,575 ሰዎችን ተጠቃሚ አድርጓል።
- በጭናቅሰን (ሱማሌ ክልል) እና በቱሊጉሌድ (ኦሮሚያ ክልል) ውስጥ የሚገኙ የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ተቋሚትን የውሀ አገልግሎት አውታርን አድሷል።
- በኦሮሚያ ክልል በጫሎና ሮጌ ቀበሌዎች ውስጥ የጤና ኬላና የእንሰሳት መድሀኒት ቤት በመገንባት10,000 ሰዎችን ተጠቃሚ አድርጓል።

## የአካል ጉዳተኞች

እአአ ከጥር እስከ ታህሳስ 2020 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ የዓአቀመኮ



የዓአቀመኮ የነቀምቴ የአካል ጉዳተኛ ሠራተኛን በክራንች አመራረት ሂደት ሲያሰተምር፤ ኦሮሚያ ክልል (2020 ዓ.ም)።

- በኦሮሚያ፣ አማራ፣ ሐራሪ፣ ደቡብ ኢትዮጵያ፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝና ሱማሌ ክልሎች ውስጥ ለሚገኙ ዘጠኝ የአካል ጉዳተኛ ማቋቋሚያ አጋር ማዕከሎች ቋሚ የእጅ መታጠቢያዎች፣የንጽህና መገልገያ ቁሳቁስና የኮቪድ መከላከያ መረጃ መልዕክቶችን የያዙ ፖስተሮች አሰራጭቷል።
- ከኢትዮጵያ ብሔራዊ የአካል ጉዳተኞች ማህበር ፌዴሬሽን ጋር በመተባበር ስለ በሽታው ያላቸውን ግንዛቤ ለማዳበርና የባህሪ ለውጥ ለማምጣት የሚያሰችሉና በአራት ዋና ዋና ቋንቋዎች የተዘጋጁ መልዕክቶች በክልልና ብሔራዊ የሬዴዮና ቴሌቪዥ'ን ጣቢያዎች አማካኝነት ለአካል ጉዳተኞች እንዲሰራጩ አድርጓል።
- አምስት የአካል ጉዳተኛ ማቋቋሚያ ማዕከሎች በሆስፒታልና ማግለያ ማዕከሎች የሚሰሩ የጤና ባለሙያዎች የሚጠቀሙበት 4,000 ጭምብሎችን (face masks) በአገር ውስጥ ለማምረት የሚያስችል ድጋፍ አድርጓል።
- 6,438 የአካል ጉዳተኞች የዓአቀመኮ እርዳታ በሚያደርግላቸው አስር የአካል ጉዳተኛ ማቋቋሚያ ማዕከሎች ውስጥ አገልግሎቱን እንዲያገኙ አድርጓል። ከእነዚህም መካከል በአነስተኛ ገቢ የሚተዳደሩ 41ዱ የአካል ጉዳተኞች አገልግሎቱን በሚያገኙበት ወቅት የዓአቀመኮ የመጓጓዣና የምግብ ወጪያቸውን ሸፍኖላቸዋል።
- ለ 32 ታራሚዎች አጠቃላይ የአካላዊ መልሶ ማቋቋም ድጋፍ አድርጓል፤ ይህም የሰው ሰራሽ አካልና የአካል ድጋፍ እንዲሁም ክራንችና ዊልቼር መስጠትን ያካትታል።

## የሰብዓዊነት ህጉን ማስተዋወቅ/ኮሚኒኬሽን

እአአ ከጥር እስከ ታህሳስ 2020 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ የዓአቀመኮ

- ከኦሮሚያ ክልል ፖሊስ ኮሚሽን ለተውጣጡ 35 የፖሊስ የወንጀል ምርመራ ሀላፊዎችና ሰራተኞች በዓለም አቀፍ የሰብዓዊነት እና ሰብዓዊ መብት መስፈርቶች ላይ ያተኮረ (ከወንጀል ምርመራ ጋር በተገናኘ መልኩ) ስልጠና አዘጋጅቷል።
- ከሱማሌ ክልል ፖሊስ ኮሚሽን ለተውጣጡ 40 ልዩ ፖሊስ ሀይል አባላት በዓለም አቀፍ የሰብዓዊነት ህግና ሰብዓዊ መብት መስፈርቶች ላይ ያተኮረ (ከሀይል አጠቃቀም ጋር በተገናኘ መልኩ) ስልጠና ሰጥቷል።
- ከሱማሌ ክልል ፖሊስ ኮሚሽን ልዩ ሀይል እንዲሁም ከኦሮሚያ ክልል ፖሊስ ኮሚሽን ልዩና መደበኛ ፖሊስ ሀይል (መቀመጫቸው በነቀምት ከተማ ያደረጉ) ለተውጣጡ 77 አባላት በዓለም አቀፍ የሰብዓዊነት ህግና ሰብዓዊ መብት መስፈርቶች ላይ ያተኮረ ስልጠና ሰጥቷል።

- ከኢትዮጵያ ፖሊስ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ጋር በኮቪድ-19 ወቅት ፖሊስ ሚናውን በአለም አቀፍና አገራዊ ህጎች መሠረት መወጣት እንዲችል እንዲሁም ማህበረሰቡ ስለበሽታው ያለውን ግንዛቤ ለማዳበር የሚረዱ መረጃዎችን የፖሊስ ሚዲያን በመጠቀም ለማሰራጨትና ድጋፍ ለማድረግ የሚያስችል የመግባቢያ ሰነድን በብቃት ተግብሯል።
- የህግ አስፈጻሚ አከላት የኮቪድ 19 ወረርሽን በመቆጣጠር ረገድ ባላቸው ሚና ላይ ያተኮረ የሁለት ቀን ስልጠና ከዓአቀመኮ መንግሰታዊና መንግስታዊ ካልሆን አጋር ድርጅቶች ለተውጣጡ 24 የሜዲያ ባለሙያዎች አዘጋጅቷል።
- በአዲሰ አበባ ዩኒቨርሲቲ በኢትዮጵያ የመጀመሪያ የሆነውን የዓለም አቀፍ የሰብዓዊነት ህግ ክሊኒክ ለማቋቋም የሚያስችል ድጋፍ አድርጓል።
- ዓለም አቀፍ የሰብዓዊነት ህግን በአገር ደረጃ ለመተግበር በሚረዱ መንገዶችና የጠቅላይ አቃቤ ህግ ጽ/ቤት በዚህ ረገድ ባለው ሚና ላይ ያተኮረ ሴሚናር ለ20 የጽ/ቤቱ ህግ አርቃቂዎችና ኤክስፐርቶች አዘጋጅቷል።
- በማህበረሰብ ውስጥ ግንዛቤን ለማዳበር የሚረዱ መሰረታዊ መርሆዎችን፣ የዓቀመኮና የኢቀመማ ተግባራትን እንዲሁም ኮቪድ-19ን ለመከላከል የተወሰዱ እርምጃዎችን በሚመለከት ከ100 በላይ መልዕክቶች በዓአቀመኮ የኢትዮጵያ ልዑክ የፌስቡክ እና የቲዊተር ገፅች ላይ እንዲወጡ ተደርጓል።

## ከኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማህበር ጋር ያለው ትብብር

እአአ ከጥር እስከ ታህሳስ 2020 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውሰጥ የዓአቀመኮ

- የ2,000 ተረጂ ሰዎች ፍላጎትን ሊሸፍን የሚችልና መሠረታዊ ቁሳቁስ የያዙ 2,000 ሳጥኖች (kits) ለኢቀመማ ሰጥቷል።
- ኢቀመማ በመጀመሪያ እርደታ አሰጣጥና የኮቭድ-19 ወረርሽኝ ግንዛቤ ማዳበሪያ ላይ ያተኮሩ ልዩ ልዩ ስልጠናዎች ለ2,261 የቀይ መስቀል በጎ ፈቃደኞችና ሰራተኞች ለማዘጋጀት የሚያስችል ድጋፍ አድርጓል።




በብጥብጥ ምክንያት ጉዳት የደረሰበት ሰው በዓአቀመኮ የዘር እህል እርዳታ

## ትግራይ ውስጥ የተደረገ ምላሽ

እአአ ከጥር እስከ ታህሳስ 2020 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውሰጥ የዓአቀመኮ

- በትግራይና አማራ ክልሎች ውስጥ ውስጥ ለቆሰሉና ለሌሎች ህሙማን የህክምና አገልግሎት ለሚሰጡ 13 የጤና ተቋማት የህክምናና የመድሀኒት እርዳታ አድርጓል። ይህም ተቋማቱ የቆሰሉና የታመሙ ሰዎችን ጨምሮ ለሌሎች 10,900 ህሙማንን ለማከም ያስችላቸዋል።
- በቅድመ ሆሰፒታል የጤና ክብካቤ ረገድ የኢቀመማ የተላያዩ ቅርጫፎች የመጀመሪያ የህክምና ሳጥኖቻቸወን መልሰው ለመሙላት የሚያስችል ተጨማሪ የህክምናና የመድሀኒት አቅርቦት አድርጓል።
- ከኢቀመማ ጋር በመተባበር 2,053 ቤተሰቦች ከተነጠሏቸው የቤተሰብ አባላቸው ጋር መልሰው ግንኙነት ለማድረግ እንዲችሉ የነጻ ስልክ ጥሪና ደህና ነኝ የሚል የቃል መልዕክት እንዲያሰተላልፉ እገዛ አድርጎላቸዋል ።
- በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል በተፈጠረው ሁኔታ የታሰሩ ሰዎች ያሉበትን ሁኔታንና አያያዛቸውን ለመዳሰስ እንዲችል የታሰሩ ሰዎችን ጎብኝቷል።
- ለኢቀመማ ሰሜን ጎንደርና ሰሜን ወሎ ቅርንጫፎቹ የቆሰሉ እና የታመሙ ሰዎችን ለማመላለስ የሚጠቀሙበትን አምቡላሶች የነዳጅ ወጪ ለመሸፈን እንዲችሉ የ719,000 ብር እርዳታ አድርጎላቸዋል።

አድራሻ

Facebook.com/ICRC AFRICA
twitter.com/ICRC_Africa
Instagram.com /icrc.afrique

ዓለም አቀፍ ቀይ መስቀል ኮሚቴ
አዲስ አበባ ዋና መስሪያ ቤት
ቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 12/13
ፖ 5701
ስ 011647 8300
ፋ 011647 8301
ኢ-ሜይል: addis_abeba@icrc.org
Facebook.com/ICRCEthiopia
www.icrc.org

ነቀምት
ቀ 05, H.No. 290
ስ +251 576 606 655
ፋ +251 576 606 657

መቀሌ
ወ. ደቡብ, ቀበሌ 16
ስ +251 344 40 8353
ፋ +251 344 40 4540

ጅግጅጋ
ዞን 2 ቀ 10, ቤ.ቁ 0196
ስ +251 252 78 8149

የዓአቀመኮ በዓለም ዙሪያ በትጥቅ ግጭትና በሌሎች ብጥብጦች ምክንያት ጉዳት ለደረሰባቸው ስዎች ሰብዓዊ ክብራቸው እንዲጠበቅና የሚደርስባቸውን ስቃይ ለመቀነስ የሚችለውን ሁሉ ያደርጋል። ይህን የሚያደርገው በአብዛኛው ከቀይ መስቀልና ቀይ ጨረቃ ማህበራት ጋር በመተባበር ነው። እንዲሁም ድርጅቱ በግጭት ምክንያት ሊደርስ የሚችለውን ተፅዕኖ/ስቃይ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊነት ህግን በማራመድና በማጠናከር እንዲሁም ዓለም አቀፍ የሰብዓዊነት መርሆዎችን በደንብ እንዲታወቁ ጥረት ያደርጋል።

ICRC